# *እምነታችንን ማሳደግ*

- እምነት - የመንፈሳዊ ህይወታችን እንዲሁም ዕድገታችን መሠረት (Foundation) ነው።
  - ሌሎቹ ፀጋዎች ሁሉ በእምነት ላይ የሚጨመሩ ናቸው።
  - የክርስቶስን በህሪ ለመውረስ በሌሎች ፀጋዊች ከማደጋችን በፊት የእምነታችን መሠረት የፀና መሆን አለበት።
  - የለበለዚያ ጌታ ኢየሱስ እንደተነገረው "በዐለት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ቀርቶ በአሸዋ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

## *እምነት ምንድነው?*

"እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው።" ዕብ11፡1

1. የክርስቲያኖች ተስፋ ምንድነው? (ምሳሌ)
   - ኢየሱስ ክርስቶስ ደግም በክብር ይመጣል። *"… የተባረከ ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንን የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገላጥ በመጠባበቅ ነው።"* (ቲቶ2፡13)
   - ሙታን እንደሚነሱ - *"እኔም እንደነዚህ ሰዎች ሁሉ ጻድቃንና ሃጥአን ከሙታን እንደሚነሱ በእግዚአብሔር ተስፋ አለኝ።"* (ሐዋ24፡15)
2. የማናየውን ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት
   - የእግዚአብሔር መኖር -*"እርሱ ብቻ የማይሞት ነው። ሊቀረብ በማይቻል ብርሃን ውስጥ ይኖራል። እርሱን ያየ ማንም የለም ሊያየውም የሚችል ማንም የለም።" (1ጢሞ6፡16)*
   - ዓለም እንዴት እንደተፈጠረች - *" ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተፈጠሩ በእምነት እንረዳለን። ስለዚህ የሚታየው ነገር የተፈጠረው ከሚታየው እንዳልሆነ እንገነዘባለን።"* (ዕብ11፡3)
3. አባቶችም የተመሰከረላቸው በዚህ ነው።"
   - አቤል - በእምነት ጻድቅ ሆነ
   - ሄኖክ - በእምነቱ ሥጋዊ ሞትን ሳያይ ተወሰደ።
   - ኖህ - ገና ስለማይታየው ነገር እግዚአብሔርን በመታዘዝ - እግዚአብሔርን ስለተነገረው ቃል በማመን - ዓለምን ከጠፈው ውሃ ደነ (ጻድቅ ወራሽ ሆነ - ለእግዚአብሔር የተለየ ሰው ሆነ)
   - የእምነት አባቶች እና እናቶች የሆኑት - አብረሃም፣ ሳራ፣ ይሳቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ - እግዚአብሔር ቃል ከዳን የገበላቸውን - ላለዩት ነገር - እግዚአብሔር አመኑ
   - በእምነት ዓለምን፣ የተፈጥሮን ህግ እንኳን ሳይቃር አሸነፉ።
     - የሙሴ ወላጆች - ህፃኑ ለእግዚአብሄር ክብር የተወለደ መሆኑን ስለተመለከቱ - በእምነት ሸሸጉት
     - ሙሴ - ወደ ፍት ልመጣ የለውን ክብር ስለተመለከተ - የፈርዖን ልጅ መባልን በእምነት እምቢ አለ።
     - በእምነት - የእሥራኤል ህዝብ ቀይ በህርን ተሻገረ - የኢያሪኮን ግንብ አፈረሱት
   - ስለ ጌዴዎን፣ ሳምሶን፣ ደዊት፣ ሳሙኤል፣ እንዲሁም ስለ ነቢያት መዘረዘር ይቻለል።
     - እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆኑም ከእነርሱ ማንም የተስፋውን ቃል የተቀበለ የለም።
     - ነገር ግን በህይወታቸው ዘመን የላዩትን - ክርስቶስ ደግመኛ ስመጣ ዋጋቸውን ይቀበላሉ።

# እምነታችን እንዴት ያድጋል?

1. የእምነት ህይወታችን የሚጀምረው፡
   - እግዚአብሔር እንዳለ በፍፁም ልብ ማመን- መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ህያው ቃል እንደሆነ ማመን።
   - ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ፣ እረሱ ስለ እኛ ሥጋ ለብሶ እንደመጣ፣ ለእኛ እንደተሰቃየና የመስቀል ሞትን እንደሞተ፣ ሞትን ድል ነስቶ በመነሳቱ በደሙ በተደረገ ቤዛነት በርሱ በማመን የሃጢአትን ይቅርታ እንዳገኘን፣ ደግም ልፈርድ እንደምመጣ ማመን አለብን።
   - ምንም እንኳን እግዚአብሔርን ያየ በይኖርም፣ እግዚአብሔር በቃሉ የተመነ አምላክ እንደሆነ ማመን።
   - እግዚአብሔር <u>በእውነት</u> ለታመኑት፣ ለምፈልጉት፣ ለሚታዘዙት፣ የተስፋውን ቃል <u>ተግተው</u> ለሚጠባበቁት በህይወታቸው የቀደውን ይፈፅማል።
   - በህይወታችን ውስጥ የተተመ፣ የሚያድግ፣ የሚያብብ፣ እየጨመረ የሚሄድ፣ እምነት ከለን፣ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ሁሉን ነገር ማድረግ እንችላለን።

2. እምነታችን ደግሞ ልያድግ የምችለው በእግዚአብሔር ቃል አማከኝነት ነው።(ሮሜ10፡17)
   - እግዚአብሄር በቃሉ ለምድራዊ ህይወታችን የሚሆኑ ብዙ ቃል ክዳኖችን ለአማኞች ሁሉ ሰጥቷል። (ስለ ቤታሰብ፣ ልጆች፣ ስለ ትደር፣ ስለ ምድራዊ ደስታ፣ ስለ ገንዘብ፣ ስለ ሰላም…)
   - እግዚአብሄር በቃሉ ተስፋ ላይ እንደ እግዚአብሄር ልጆች ሆነን ብንጠይቅ - እግዚአብሄር እርሱ በፈቀደውና በአቀደው ሰዓት በህይወታችን ይሆናሉ።
   - ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀው ተስፈችንን ማወቅና እግዚአብሄርን ደስ በሚያሰኘው መንገድ መመላለስ ብቻ ነው።

3. በመጨረሻም ይህንን ሁሉ እየደረግን የእምነት ሩጫ መሮጥ ያስፈልጋል።(ሉቃ21፤34-36፣ ማር4፡19)፣ (ቆላ3፡8፣ 1ጴጥ2፡1-2፣ ያዕ1፡21) (ቆላ3፡1-2)

- በጀርባችን የየዝነውን ጭነት፣ መውረድ ያለበትን ነገር ማውረድ አለብን።
- አንድ አይነት ሩጫ መሮጥ አለብን። (የልፈጠነም፣ የልዘገየም) - የመራቶን ሩጫ እንጂ - የአጭር ርቀት ሩጫ እንደምሮጥ ስው መሆን የለብንም።
- አይናችንን በጌታ ላይ መሆን አለበት።
- ኢየሱስ እንዴት መስቀልን ብቻ ሳይሆን ከመስቀል በፍት የነበረውን ፈተና እንዴት እነደተወጣ ከሱ መማር አለብን።